# የኢትዮጵያ ሥልጣኔ መነሻው ፥ ጉዞውና መድረሻው

## ጌታቸው ኃይሌ

### መግቢያ ፤

የዓባይ ወንዝ ከምንጩ ላይ ትንሽ ነው ፤ ከብዙ የኢትዮጵያ ታላላቅ ወንዞች አይበልጥም ። ኢትዮጵያን ሲለቅ ግን ግዙፍ ሆኖ ነው ። ምንም እንኳ"ዓባይ" ቃሉ አንስታይ ጾታ ("ትልቂት" ማለት) ቢሆንም ወንዙ በዚህ ስም የተጠራው ይኸንን ትልቅነቱን ለማመልከት ሳይሆን አይቀርም ።

የዓባይን ግልገልነትና ዓቢይነት ያነሣሁት  ለሥልጣኔያችን ልደትና እድገት ምሳሌ እንዲሆነኝ ነው ። የኢትዮጵያ መንግሥት ይዞት የሚጓዘው ሥልጣኔ የተወለደው የኢትዮጵያ መንግሥት እተወለደበት ቦታ ነው ፤ ጽራዕ ወይም ትግራይ ውስጥ ማለቴ ነው ። ሥልጣኔው በዚያና በዚህ ተጉዞ ፥ ተጉዞ  እየዳበረ መንግሥታዊ ማእከላችንን አዲስ አበባ ላይ ካደረግነው ከእኛ ዘመን ደርሷል ። የዓባይ ወንዝ ሲጓዝ ከየቦታው የሌላ ወንዞች ውኻ እየተመገበ እንደገዘፈ ሁሉ ፥ የኢትዮጵያ ሥልጣኔም መንግሥት እጁን ከዘረጋበትና ማእከሉ ካደረገበት ቦታ ሁሉ ምግብ እያገኘ ገዝፏል ። መግዘፍ ብቻ ሳይሆን መልኩም በመጠኑም ቢሆን ተለውጧል ። ለምሳሌ ፥ ቀጣዩ ሥልጣኔ ሲጀመር በሕዝብና በመንግሥት ደረጃ የመጻጻፊያው ቋንቋ ግዕዝ ነበር ፤ ቀጥሎ አማርኛ ሆኗል ። ይኸ አንድ ግዙፍ ለውጥ ነው ። ግን ጨርሶ ሙጥጥ ብሎ አልተለወጠም ፤ ሊሆንም አይችልም ። ባህል ሙጥጥ ብሎ አይለወጥም ። የግዕዝ ቋንቋ ቢዳከምም ፊደሉ ቀጥሏል ፤ ቋንቋውም በሰፊው የሚሠራበት ቦታ አለ ።

ሥልጣኔ ሰው-ሠራሽ ስለሆነ ፥ ስለኢትዮጵያ ሥልጣኔ ስጽፍ ስለባለቤቶቹ ማንነት መጻፍ የግድ ይሆናል ።

### የሥልጣኔያችን ባለቤቶች ፤

የዚህ የኢትዮጵያ ሥልጣኔ ባለቤቶች እነማን ናቸው?  "ሥልጣኔው የዳበረው መንግሥት እጁን ከዘረጋበትና ማእከሉ ካደረገበት ቦታ ሁሉ ምግብ እያገኘ ነው" ካልን ፥ ባለቤቶቹ መንግሥት እጁን በዘረጋበትና ማእከሉ ባደረገበት ቦታ ሁሉ የሚኖሩ ሰዎች ሁሉ ናቸው ። ምንጮቹ የመዘገቡትን የአክሱምን ፥ የአደፋን (የላስታን) ፥ የመርዓዴን (የአምሐራ-ሸዋን) ፥ የጎንደርን ፥ የአዲስ አበባን አስተዋፅዖ ማን ይክዳል? መነሻው ፥ እድገቱና መድረሻውስ አይካድም ፤ ግን ማን ወለደው?

ልደቱ ትግራይ ውስጥ ከሆነ ወላጆቹም እትግራይ ውስጥ ነበሩ ማለት ነው ። ግን ትግራዮች ነበሩ ማለት ነው? "የጎንደርና የአዲስ አበባ ሥልጣኔ የጎንደርና የአዲስ አበባ ተወላጆች ሥልጣኔ ነው" ካልን የአክሱምን

ሥልጣኔም የወለዱት የትግራይ ተወላጆች ናቸው ማለት ይቻላል ። ሊሆንም ይችላል ፤ ሆኖም ፥ የታሪክ ሂደት እንዲህ አይደለም ። አንድ ከተማ ሲመሠረት ባህልንና ሥልጣኔን ለማዳበር ከተወላጆቹ ይልቅ መጤዎቹ ያመዝናሉ ። ከተማ የሩቅ ሰዎችን እንደ ማግኔት ይስባል ። ጀርመኖች "በበርሊን ከተማ የተወለደ በርሊናዊ የለም" የሚል ተረት ያላቸው ስለዚህ ነው ። ለምሳሌ ፥ አክሱም ላይ የሳባውያን ሥልጣኔ ዳብሮ ነበር ። የሳባውያንን ቋንቋና ሥልጣኔ አዳባሪዎቹ የጠፉት ሳባውያን እንጂ ፥ ትግሬዎች አልነበሩም ። ቢሆኑ ኖሮ ፥ ቋንቋቸውን ይወርሱ ነበር ። ትግርኛና ሳብኛ የተለያዩ ቋንቋዎች ናቸው ። ሳባውያን ባህላቸውን ለማንም ሳያወርሱ ጠፍተዋል ።

ሳባውያን ከነቋንቋቸው ከጠፉ በኋላ ፥ የሥልጣኔያችን አስኳል የተተካው ግዕዝ በሚባለው የአግዓዝያን ቋንቋና ይዞቱ ነው ። ግዕዝ ኢትዮጵያ ውስጥ ከነበሩት ብዙ ቋንቋዎች አንዱ ነበረ ። ባለቤቶቹ አግዓዝያን ይባሉ ነበረ ። የኢትዮጵያም ስም ብሔረ ግዕዝ ነበረ ። (ኢትዮጵያ የሚለውን ስም አገራችን የግሏ ያደረገችው በኋላ ነው ።) አገሪቷ በስማቸው የተጠራችው ያለምክንያት አይደለም ፤ (ሳባውያንን አጥፍተው ወይም ተክተው) ያቀኗትና የወረስነውን የመንግሥት ሥልጣኔ የፈጠሩት እነሱ ቢሆኑ ነው ። "ቋንቋቸውን የጽሑፍና የዕውቀት ቋንቋ ያደረጉትም ቀደም ብለው ብሔራዊ ቋንቋ እንዲሆን ስላደረጉት ነው" ለማለት ይቻላል ። "እንዲሆን አደረጉት" ማለት ሁኔታውን አመቻቹለት ማለት ነው እንጂ ፥ "ሕግ አወጡለት ፥ ዓዋጅ አስነገሩለት" ማለት አይደለም ። ሕግ ሳይወጣለት ፥ ዓዋጅ ሳይነገርለት የሕዝብ ተቀባይነት እንዳገኘው እንደ አማርኛ ማለት ነው ። ሁኔታ ስለተመቻቸለት ፥ ሌላ ቋንቋ የሚናገሩም ለመጻፍና ዕውቀት ለማግኘት ሲፈልጉ የአግዓዝያንን ቋንቋ እየተማሩ በእነሱ ቋንቋ በግዕዝ ይጽፉ ነበር ። ይህም ትግራዮችን ፥ አገዎችን ፥ አማሮችን ፥ ሌሎችንም ይመለከታል ። በአፍ መፍቻ ቋንቋ ላይ ብሔራዊ ቋንቋ ተምሮ በዚያ ቋንቋ መማርና መጻፍ አዲስ ነገር አይደለም ።

ለመሆኑ ፥ አገር አቅንተው ቋንቋቸውንና ሥልጣኔቸውን ያወረሱን አግዓዝያን እነማን ነበሩ? ልጆቻቸው አሁንስ አሉ ወይ? አግዓዝያን ከብዙ ነገዶች አንዱ እንደነበሩና አገር አቅንተር ሥልጣኔ መሥርተው አሁን እንደጠፉ እንጂ ፥ ከዚህ የበለጠ ስለእነሱ የሚታወቅ ነገር የለም ። ግን አንድ ነገድ ጠፋ ሲባል "ልጆቻቸው የአባቶቻቸውን ቋንቋ መናገር አቆሙ" ማለት ነው ። በኢትዮጵያ ውስጥ እንደ ሳባውያን ፥ እንደ ጋፋት ፥ እንደሃርላ ያሉ ብዙ ነገዶች ጠፍተዋል ። አግዓዝያንም እንደነሱ ጠፍተዋል ። "የሉም ፤ ጠፍተዋል" ስንል "ዛሬ በግዕዝ ቋንቋ አፉን የሚፈታ ነገድ የለም" ማለታችን ነው እንጂ ፥ "ደማቸው ከምድረ ኢትዮጵያ ደርቋል" ማለት አይደለም ። ሥልጣኔያቸውን እወረስነው ደም ውስጥ አለ ።

ሥልጣኔያቸውን ሁላችንም እኩል ወርሰን እኩል አዳብረነዋል ። ይኸም በዓሥራ ስድስተኛው ምእት ዓመት ወደማህል ኢትዮጵያ የገቡትን ኦሮሞኛ ተናጋሪዎችን አስተዋፅኦ ይጨምራል ። አሁን ካሉት የኢትዮጵያ ነገዶች ውስጥ አንዱ ተለይቶ "የአግዓዝያን ልዩ ወራሲ እኛ ነን" ሊል አይችልም ። ልንል የምንችለው "ግዕዝን የሚመስል ቋንቋ ያላቸው ነገዶች ሁሉ ዘመዶቻቸው ናቸው" ማለት ብቻ ነው ። ቋንቋቸውን ቀድሞ ይዞና በይበልጥ መጠቀም በቀጥታ ወራሲነት መብት ይሰጡ ቢሆን ግን አማርኛ

ተናጋሪዎችን ማንም አይቀድማቸውም ። ምክንያቱም ፥ ከግዕዝ ቀጥሎ በግዕዝ ፊደል የተጻፈ አማርኛ ነው ። አማርኛ በግዕዝ መጽጻፍ የተጀመረው ዛሬ አማርኛ የሚናገሩ ሰዎች በሚኖሩበት አካባቢ ብቻ አይደለም ። በትግራይ ውስጥም ይጻፍበት እንደነበረ ከትግራይ ክፍለ ሀገር የሚመጡ የጥንት መጻሕፍት ላይ የሚገኙ የኅዳግ ላይ ማስታዎሻዎች ይመሰክራሉ ። ማስታወሻዎቹ ተጻፉት ወይ በግዕዝ ወይ በአማርኛ ወይ በሁለት ቋንቋዎች ድብልቅ ነው ።

## የቋንቋዎች አከፋፈል ፤

እስከዛሬ ያለው የቋንቋ ተመራማሪዎች የሰጡን የኢትዮጵያ ቋንቋዎች አከፋፈል መከለስ ያለበት ይመስለኛል ። ሊቃውንቱ የሚከፋፍሏቸው የሴም ፥ የኩሽ ፥ የዓባይ አካባቢ (Semitic, Cushitic, Nilotic) ብለው ከሦስት ቦታ ነው ። እስከቅርብ ጊዜ ድረስ የዓባይ አካባቢ (Nilotic) ይባል የነበረውን "የኦሞ አካባቢ (Omotic) ብለውታል ።

የሴም ቋንቋዎች የሚሉት ግዕዝን ፥ ትግረን ፥ ትግራይን ፥ አማርኛን ፥ ጉራግኛን ፥ . . . ሲሆን ፥ የኩሽ ቋንቋዎች የሚሉት ሱማልኛን ፥ ኦሮምኛን ፥ አገውኛን ፥ ቢሌንኛን ፥ . . . ይጨምራል ። እንደሚታየኝ የሴምና የኩሽ ቋንቋዎች በአንድነት የሚታዩ ፥ ተናጋሪዎቻቸውም ከሞላ ጎደል እኩል የሚቀራረቡ ናቸው ። እንዲህ ከሆነ ፥ ሁለቱን የሚያቀራርብ አንድ የሚያደርግ አዲስ ስም ሊወጣላቸው ወይም ሁለቱም ሴማዊ (Semitic) ሊባሉ ይገባል ። በበኩሌ ሁለቱም ሴማዊ (Semitic) ቢባሉ እመርጣለሁ ። ይኸንን አዲሱን አቋሜን የሚደግፈው ምርምሮቹ የሚያሳዩት የቋንቋዎቹ ተመሳሳይ ሂደት ብቻ ሳይሆን ፥ አንድ የጀርመን የምርምር ቡድን ስለሱማሌዎች ያደረገው የጥናት ውጤት ጭምር ነው ። የምርምሩ ውጤት ሱማሌዎችን በጥንት ዘመን ከደጋው የኢትዮጵያ ምድር ወደቆላር የወረዱ የማህል ኢትዮጵያ ሰዎች ያገርጋቸዋል ።

ሁለቱን አንድ አድርገን በአንድ ስም (ሴማዊ Semitic) ካልናቸው ፥ "ኩሻዊ" (Cushitic) የሚለውን አጠራር ምን እናድርገው? እሱ ለባለቤቶቹ መሰጠት ይኖርበታል ። ባለቤቶቹ እነማን ናቸው? "ኩሽ" የሚለው ስም የመጣው ከዕብራይስጡ መጽሐፍ ቅዱስ ነው ። ዕብራይስጡ "ኩሽ" የሚላቸው ጥቁሮችን ነው ። ዕብራይስጡን "ኩሽ" ግሪኩ "ኢትዮጵያውያን" ይላቸዋል ። እኛ መጽሐፍ ቅዱስን የተረጐምነው ከግሪክ ስለሆነ የዕብራይስጡን "ኩሽ" እንደግሪክኛው "ኢትዮጵያውያን" እያልን ተረጐምነው ። የቆዳን ጥቁረት ስለሚያመለክት ፥ እውነተኞቹ የስሙ ባለቤቶች ፥ ኢትዮጵያውያን (ዛሬ ኤርትራውያን የተባሉት ጭምር) ሻንቅላ የሚሏቸው ናቸው ። የዕብራይስጡ "ኩሽ" እና የግሪኩ "ኢትዮጵያውያን" እነሱ ናቸው ። የቋንቋ ተመራማሪዎች "የዓባይ አካባቢ" (Nilotic) የሚሏቸውም እነሱን ነው ። መጽሐፍ ቅዱሱ ግዮንን "መላ ኢትዮጵያን የሚያጠጣው ወንዝ ነው" ካለና እኛ ደግሞ "ግዮን ዓባይ ነው" ካልን ፥"ኩሻዊ" (Cushitic) የሚለው ስም "የዓባይ አካባቢ" ኢትዮጵያውያን መጠሪያ መሆንና "የዓባይ አካባቢ"(Nilotic) የሚለው

አጠራር መውደቅ አለበት ። ይኸ አስተሳሰብ የኢትዮጵያን ቋንቋዎችና ተናጋሪዎቹን ከሁለት ቦታ ብቻ ይከፍላቸዋል ።

ቋንቋና ዘር ፤

ከቋንቋ ጋር ተያይዞ የሚመጣ ነገር "ዘር" ነው ። ምዕራባውያን race የሚል ቃል ፈጥረው የሰው ልጆች የተለያዩ ዘሮች እንደሆኑ ይናገራሉ ። በእኛ አስተሳሰብ ግን ይኸ ቦታ የለውም ። ቃሉ በግዕዝም ሆነ በአማርኛ ቋንቋ የለም ፤ የሰው ልጅ ዘር አንድ ነው ፤ የተለያየ ነው አንልም ። እርግጥ ሲቸግረን race የሚለውን ቃል "ዘር" በሚለው ቃል እንተረጉመዋለን ፤ የችግር ነው እንጂ ፥ ስሕተት ነው ። እንዲያውም አተረጓጐሙ ጉዳት አለው ። ምክንያቱም "እገሌ የእገሌ ዘር ነው" የሚለውን ንጹሕ አነጋገር መጥፎ ትርጒም ይሰጠዋል ። "ዘር" የሚለውን የምንጠቀምበት ስለ ሰው ዘር ከሆነ ፥ ወደ እንግሊዝኛ ሲተረጐም seed; scion እንጂ ፥ race አይሆንም ። እግዚአብሔር ለቅዱስ ዳዊት "መንበርህ ከዘርህ አይወጣም" ብሎ ተስፋ ሲሰጠው ፥ "ከሥጋህ ተዘርቶ ከተወለደው ልጅህ አይወጣም" ማለቱ ነው እንጂ ፥ "ከሌሎች ከተለየ ዘርህ (race)" ማለቱ አይደለም ። ማንም ሰው የአባቱ ዘር ነው ። ሁለት ወንድማማቾች የየራሳቸው ዘር አላቸው ። ሆኖም ዘሮቻቸው የተለያዩ races አያደርጋቸውም ።

በቋንቋ ተመርቶ የኢትዮጵያን ሕዝብ ለመከፋፈል መሞከር ለፖለቲካ መጠቀሚያ ካልሆነ መሠረት አልባ ሙከራ ነው ። ከዛሬዎቹ ኢትዮጵያውያን መካከል የጥንት አባቶቹን ቋንቋ የሚናገር ቢገኝ የሚደነቅና ለሚዩዝየም ፥ ለላንቲካ የሚንከባከቡት ፍጥረትይሆናል ። አማርኛ ተነጋሪ ሁሉ የጥንት አባቶቹ አማሮች ነበሩ የሚል አላዋቂ ብቻ ነው ። ኦሮምኛ ተናጋሪ ሁሉ አባቶቹ ኦሮሞዎች ነበሩ የሚል የኢትዮጵያን ሕዝብ ታሪክ የማያውቅ ብቻ ነው ። የጠፉት ነገዶች ደማቸው ወደዛሬዎቹ ኢትዮጵያውያን ደም ተዛውሯል ፤ ሥልጣኔያቸውንም ወርሰናል ካልን ፥ እኛ የዛሬዎቹ ኢትዮጵያውያን የብዙ ነገዶች ውጤት ነን ።

"ዘርንና ቋንቋን ሳናገናኝ በቋንቋ ብቻ ተመርተን እንከፋፍላቸው" ቢባል ይቻል ይሆናል ፤ ግን የተለያየ ቋንቋ የሚናገሩ ብዙ ሕዝቦች ስላሉን ፥ ከማይፈታ ችግር እንገባለን ። አንደኛ ክፍያውን አንዘልቀውም ፤ ከሰባ ያልፋል ። ብንዘልቀውስ ከሰባ የሚበልጠውን ክፍልፍል ምን እናድርገው? ሰባውንም ራሳችሁን አስተዳድሩ ለማለት ነው? ሁለተኛስ በቋንቋ የተከፋፈሉት ሕዝቦች አማራ ፥ ኦሮሞ ፥ ትግራይ ፥ ጉራጌ ፥ ወዘተ ካልሆኑና በነዚህ ስሞች ካልተጠሩ በምን ሌላ ስም እንጥራቸው?

በቋንቋ የመከፋፈል ሐሳብ የተጸነሰው ትግርኛ ፥ ኦሮምኛ ፥ ሱማልኛ ከሚናገረው ሕዝብ የወጡ ፖለቲከኞች ፥ "አማራ አይገዛንም" ብለው የአመፁ ጊዜ ነው ። ዓመፅ ሲጀምሩም ሆነ ዛሬ ፥ አማርኛ ፥ ትግርኛ ፥ ኦሮምኛ ፥ ሱማልኛ የሚናገሩ ሕዝቦች እንጂ ፥ አማራ ፥ ኦሮሞ ፥ ትግሬ ፥ ሱማሌ የሚባል ዘር እንደሌለ አያውቁም ። ሁለተኛም ፥ እነሱ ያዩት ክልል መያዛቸውን ያንን ክልል መግዛታቸውን እንጂ ፥ በያዙት ክልል ውስጥ ሌላ ቋንቋ ለሚናገሩ ደንታ የላቸውም ። እነሱ "አማራ አይገዛንም" እንዳሉት ፥

በሚይዙት ክልል ውስጥ ያሉት ሌላ ቋንቋ ተናጋሪዎችም ፥ "ትግሬ ፥ ኦሮሞ ፥ ሱማሌ አይገዛንም" ሊሉ እንደሚችሉ ልብ አላሉትም ፤ ቢሉትም ለራሳቸው የማይቀበሉትን መፍትሔ አስበውላቸው ይሆናል ።

"ሕዝብ" እና "ሕዝቦች" ፤

ከቋንቋና ከዘር ጋር የተያያዘ ችግር ፥ "ሕዝብ" የሚለው ቃል ትርጉም ነው ። ቃሉ "ሕዝቦች" ተብሎ ሲበዛ ያስደነግጠናል ። ግን "ሕዝብ" የሚለውን ቃል ሲወርድ ሲዋረድ በደረሰን ትክክለኛ ትርጉሙ ከተቀበልነው ፥ የብዙ ቍጥሩ (ሕዝቦች) ሊያስደነግጠን አይገባም ። "ሕዝብ" የሚያመለክተው በአንዳች ምክንያት የተገናኘውንና የተሰባሰበውን የሰው ብዛት ነው ። ሰው ለወሬ ይሰበሰባል ፤ በዓል ለማክበር ይሰበሰባል ፤ ለመዝመት ይሰበሰባል ። ስብስቡ ሕዝብ ይባላል ። "ዛሬ ብዙ ሕዝብ ተሰብስቦ ነበር" ይባላል ። በቋንቋ ፥ በሃይማኖት ፥ በቀየ የሚገናኝ ሕዝብ አለ ። ከሁሉም በላይ ደግሞ የአንድ አገር ሕዝብ አለ ። እንዲህ ከሆነ ፥ በአንድ አገር ሕዝብ መካከል ብዙ ሕዝቦች አሉ ማለት ነው ። እነሱ ራሱን የቻለ አንድ አገር ሕዝብ አይባሉም ። በአንድ ሀገር ሕዝብ መካከል ራሱን የቻለ ሀገር የለም ፤ ሊኖርም አይችልም ። አንድ ሕዝብ ራሱን የቻለ አገር ሕዝብ ለመሆን ረጅም የታሪክ ጉዞና የተለያዩ መስፈርቶች ማስመዝገብ ይኖርበታል ።